# ፍርድ አዋቂ ካለ?

በጭን'ቅ በመከራ ፣ በሀዘን ተውጦ
ሞት ከሚሉት ጋራ ፣ ፊት-ለፊት ተጋፍጦ፤
በዛም - በዚህ በሎ ፣ ጎሊናውን ሽጦ
በረሀ - ውቅያኖስ ፣ ኬላውን አቋርጦ፤
"ገላ...." ተሰደደ ፣ ሄደ ባህር ማዶ
"ልብ...." ኋላ ቀረ ፣ ሀገር ቤቱን ወዶ ።

ታድያ ምን ያደርጋል ፣ የሁለት ዓለም ሰው
ስጋውን ነው እንጂ ፣ ነፍሱን አይደልለው።

እናማ..... እናትሀገር ፣ የምልሽ እማማ
"እህ-ህ-ህ...."፣ ሆነልሽ የ'ኔ ነገርማ ።.........

ቀንን - ቀን ሲተካው ፣ ውስጤንም ከዳውት
እኔ - እኔን ብጠይቅ ፣ ብፈልግ አጣውት።

እንድ አጭር ብርድልብስ ፣ ማጠፊያ እን'ዳጠረው
እግሬን ስሸፍነው፣ 'ራሴን በረደው ።

ፍርድ አዋቂ ካለ? ፣ እስቲ እኔን ይፍረደኝ
ልቤን ከገላዬ - ገላዬን ካ'ገሬ ፣ አስታራቂ ይስጠኝ።
-------------//-----------

ፊልጶስ / 2004
e-mail: philiposmw@gmail.com

EthioLion.Com